***የመገናኛ ብዙሃን እና ተያያዥ የንግድ ሥራ መደቦች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች***

በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት አግባብነት ያላቸው የመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች አዋጁ በሚሸፍናቸው የንግድ ሥራ መስኮች ሊሟሉ የሚገባቸውን የሙያ ብቃት መስፈርቶች በመመሪያ መወሰን ያለባቸው መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ በንግድ ሚኒስቴር እና በክልል ቢሮ ፈቃድ የሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ መደቦችን ለመወሰን በወጣው መመሪያ መሰረት ባለሥልጣኑ የሙያ ብቃት መስፈርት የሚያዘጋጅላቸው የንግድ ሥራ መስኮች በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክተዋል።

| ተ.ቁ | የዋና ዘርፍ መደቦች ባለ አንድ አሀዝ | ዋና ክፍል ባለ 3 አሀዝ | የፈቃድ መለያ መደብ | ብቃት አረጋጋጭ | ፈቃድ ሰጪ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጋዜጣ፣ መፅሄት እና በጊዜ የሚታተሙ ፅሁፎች | | 3242 | ኢ. ብ. ባ | ንግድ ሚኒስቴር |
| 2 | የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ ማስተላለፊያዎች መሳሪያዎችን መፈብረክ | 372 | 3720 | ኢ. ብ. ባ | ንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ |
| 3 | የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ መቀበያዎች፣ ድምፅ ወይም ቪዲዮ መቅጃ ወይም ማባዣ መሳሪያዎችና ተያያዥነት ያላቸው እቃዎች መፈብረክ | 373 | 3730 | ኢ. ብ. ባ | ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ |
| 4 | ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ድምፅ ማጉያዎች፣ የመቅጃ እና የምስል መቅረጫ መሳሪያዎች (ከኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክስ ምርት ውጤቶች በስተቀር) የጅምላ ንግድ | - | 61326 | ኢ. ብ. ባ | ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ |
| 5 | ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ድምፅ ማጉያዎች፣ የመቅጃ እና የምስል መቅረጫ መሳሪያዎች (ከኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክስ ምርት ውጤቶች በስተቀር) አስመጪ | - | 65326 | ኢ. ብ. ባ | ንግድ ሚኒስቴር |
| 6 | ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ድምፅ ማጉያዎች፣ የመቅጃ እና የምስል መቅረጫ መሳሪያዎች (ከኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክስ ምርት ውጤቶች) በስተቀር ላኪ | - | 66226 | ኢ. ብ. ባ | ንግድ ሚኒስቴር |
| 7 | የማስታወቂያ ሥራ | 885 | 8850 | ኢ. ብ. ባ | ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ |
| 8 | የሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ሥራዎች | - | 9613 | ኢ. ብ. ባ | የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን |
| 9 | የዜና ዘገባ ሥራ | 962 | 9620 | ኢ. ብ. ባ | ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ |

ባለሥልጣኑ በእነዚህ የንግድ ሥራ መደቦች ሊሟሉ የሚገባቸው የሙያ ብቃት መስፈርቶችን እና ነጋዴው የንግድ ሥራውን ሲያከናውን እንደሚያሟላቸው ግዴታ የሚገባባቸውን መስፈርቶች በመመሪያ መወሰን፣ የንግድ ብቃትን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስ፣ በሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ሥራ ለመሠማራት ለሚያመለክቱ አመልካቾች የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠት እና ቁጥጥር ስለማድረግ በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 44 በተመለከተው መሠረትም ባለሥልጣኑ፡-

- ✓ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠባቸው መስፈርቶች እና ግዴታዎች መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ እና
- ✓ ነጋዴው ፈቃድ ከተሰጠበት መስፈርት ውጭ መስራቱን ወይም ሕግን በመጣስ ጥፋት መፈፀሙን ካወቀ መወሰድ ስለሚገባው አስተዳደራዊ እርምጃ ለንግድ ሚኒስቴር ወይም ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው የክልል ንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ወይም ለክልል ኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ስልጣን ለተሰጠው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

ይህንንም ለማስፈፀም የመገናኛ ብዙሃን እና ተያያዥ የንግድ ሥራ መደቦች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 3/2003 ወጥቷል።

***የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች***

***ሀ. በመገናኛ ብዙሃንና ተያያዥ የንግድ ሥራ መስኮች ለመሰማራት መሟላት ያለባቸው የጋራ መስፈርቶች***

- ✓ በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት የተሰጠ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣
- ✓ አመልካቹ ግለሰብ ወይም ወኪል ከሆነ የራሱን ወይም የንግድ ማኅበር ከሆነ የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተነሳው 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ እንዲሁም የአመልካቹ፣ የሥራ አስኪያጁ እና የማኅበሩ አባላት የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የጸና ፓስፖርት ፎቶ ኮፒ፣
- ✓ አመልካቹ የንግድ ማኅበር ከሆነ የማኅበሩ መመስረቻ ፅሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የተረጋገጠ ዋና ቅጂ፣
- ✓ ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ፣
- ✓ ለሥራው አስፈላጊ የሆነ የካፒታል መጠን ያለው ስለመሆኑ ለባለሥልጣኑ ከባንክ የተጻፈ ደብዳቤ፣

***ለ. በመገናኛ ብዙሃንና ተያያዥ የንግድ ሥራ መስኮች ለመሰማራት መሟላት ያለባቸው የተናጠል መስፈርቶች***

***1. በየጊዜው በሚወጡ የሕትመት ውጤቶች (ቢጋዜጣ፣ መፅሄትና በጊዜ በሚታተሙ ፅሁፎች) ለመሰማራት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች***

- ✓ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባላቸው ሰዎች የተቋቋመና በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ማኅበር መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
- ✓ ዋና አዘጋጁ በማናቸውም የትምህርት መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ዋና እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ ወይም በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣
- ✓ አመልካቹ የንግድ ሥራውን ሲጀምር የተሟላ የሥራ ሪከርድ እና ሠነዶችን አደራጅቶ እንደሚይዝ፣ በሙያ ብቃት መስፈርቶች መሰረት እንደሚሰራ እና ለምርመራ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ እንደሚያደርግ የግዴታ ወረቀት ይፈርማል።

***2. የቴሌቪዥንና ሬዲዮ፣ ማስተላለፊያ መሳሪያዎችን በመፈብረክ እና የቴሌቪዥንና የሬዲዮ መቀበያዎች፣ ድምፅ ወይም ቪዲዮ መቅጃ ወይም ማባዣ መሳሪያዎችና ተያያዥነት ያላቸውን እቃዎች በመፈብረክ ሥራ ለመሰማራት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች***

- ✓ የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ፣
- ✓ የሰው ሀይል አደረጃጀትና የትምህርት ደረጃ በኤሌክትሪካል፣ በኤሌክትሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በዲግሪ የተመረቁና በቂ ባለሙያዎች መኖራቸውን የሚያስረዳ ሰነድ፣
- ✓ ሥራው በሰው ጤና እና ደህንነት ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርስ ስለመሆኑ አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## The Fedral Democratic Repbulic of Ethiopia

## የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን

## Ethiopia Broadcasting Authority

# የመገናኛ ብዙኃን እና ተያያዥ የንግድ ሥራ መደቦች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

ስልክ (Tel):- 251-11553-8759/60
ፋክስ (Fax):- 251-11553-6750
ኢ-ሜይል (E-mail):- e.b.a.1@ethonet.et
ዌብሳይት (Website):- www.eba.gov.et
የመ.ሣ.ቁ (P.O.Box):- 43142

- ✓ ሥራው በሰው ጤና እና ደህንነት ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርስ ስለመሆኑ አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ዋና እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ፣ በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣
- ✓ የምርት ማከማቻ መጋዘን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ እና መጋዘኑ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ ወይም በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ቤት ወይም የማምረቻ ቦታ ለንግድ ሥራው ተስማሚ፣ እሳት ከሚያስነሱ ነገሮች የራቀ እና የሌሎችን አኗኗር የማያናጋ መሆኑ፣

**በተጨማሪም አመልካቹ የንግድ ሥራውን ሲጀምር እንደሚያሟላቸው በመግለፅ የግዴታ ወረቀት የሚፈረምባቸው መስፈርቶች፡-**

- ✓ የምርቱ ምንጭ፣ የስርጭት አውታርና አስፈላጊ ገላጭ ፅሁፎች ተሟልተው መገኘታቸውን እንዲሁም የተሟላ የሥራ ሪከርድ እና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ እና ለምርመራ አስፈላጊ በሆኑበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ ማድረግ፣
- ✓ ዋስትናው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ውስጥ ጥገና ለማድረግ ዋስትና የሚሰጥ መሆኑን፣
- ✓ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል ማሽነሪ፣ ማጓጓዣ እና መጫኛ ማሟላት፣
- ✓ የመለዋወጫ ወይም ጥሬ ዕቃ ክምችት ያለው መሆን፣
- ✓ ስለመሳሪያዎች አጠቃቀም መግለጫ ወይም ማኑዋል ማዘጋጀት፣
- ✓ የምርቱን መሸጫ ዋጋ ዝርዝር በግልፅ በሚታይ ቦታ መለጠፍ፣
- ✓ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና ማድረጊያ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ✓ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ ያለው፣ እና
- ✓ የሬዲዮ እና ቴሌቪዥን መሳሪያው የጥራትና የቴክኒክ ደረጃውን ያሟላ ስለመሆኑ በእቃው ላይ የጥራት ማረጋገጫ መለጠፍ ያለበት ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምልክቱን መለጠፍ።

### 3. በሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ድምፅ ማጉያዎች፣ የመቅጃ እና የምስል መቅረጫ መሳሪያዎች (ከኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክስ ምርት ውጤቶች በስተቀር)

- ✓ የሰው ሀይል አደረጃጀትና የትምህርት ደረጃ በኤሌክትሪካል፣ በኤሌክትሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ወይም በተመሳሳይ ሙያ ቢያንስ በዲፕሎማ የተመረቀና ያለው አንድ ባለሙያ መኖሩን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ዋና እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ፣ በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣
- ✓ የምርት ማከማቻ መጋዘን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ እና መጋዘኑ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ ወይም በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ቤት ለንግድ ሥራው ተስማሚ፣ እሳት ከሚያስነሱ ነገሮች የራቀ እና የሌሎችን አኗኗር የማያናጋ መሆኑ፣

**በተጨማሪም አመልካቹ የንግድ ሥራውን ሲጀምር እንደሚያሟላቸው በመግለፅ የግዴታ ወረቀት የሚፈረምባቸው መስፈርቶች፡-**

- ✓ የምርቱ ምንጭ፣ የስርጭት አውታርና አስፈላጊ ገላጭ ፅሁፎች ተሟልተው መገኘታቸውን እንዲሁም የተሟላ የሥራ ሪከርድ እና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ እና ለምርመራ አስፈላጊ በሆኑበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ ማድረግ፣
- ✓ ስለመሳሪያዎች አጠቃቀም መግለጫ ወይም ማኑዋል አያይዞ ማቅረብ፣
- ✓ ሥራውን ለመሥራት ማጓጓዣ እና መጫኛ የሚያሟላ መሆኑን፣
- ✓ የምርቱን መሸጫ ዋጋ ዝርዝር በግልፅ በሚታይ ቦታ መለጠፍ፣ እና
- ✓ ዋስትናው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ውስጥ ጥገና ለማድረግ ዋስትና የሚሰጥ መሆኑን፣
- ✓ የምርቱን መሸጫ ወጋ ዝርዝር በመግለጽ በሚታይ ቦታ መለጠፍ
- ✓ ዋስትናው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ውስጥ ጥገና ለማድረግ ዋስትና የሚሰጥ መሆኑ

- ✓ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ ያለው እና
- ✓ የሬዲዮ እና ቴሌቪዥን መሳሪያው የጥራትና የቴክኒክ ደረጃውን ያሟላ ስለመሆኑ በእቃው ላይ የብቃት ማረጋገጫ መለጠፍ ያለበት ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምልክቱን መለጠፍ።

### *4. በማስታወቂያ ሥራ ለመሰማራት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች*

#### *ሀ. በመገናኛ ብዙሃን ማስታወቂያ የማስተላለፍ ሥራ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፡-*

- ✓ በማርኬቲንግ፣ በጋዜጠኝነት ወይም በሌላ መሰል ትምሕርት ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው አንድ ባለሙያ መኖሩን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
- ✓ አንድ ስቱዲዮ እንዲሁም ቢያንስ አንድ ፕሮፌሽናል ቪዲዮ ካሜራ፣ አንድ ፕሮፌሽናል ፎቶ ካሜራ፣ አንድ ፕሮፌሽናል የድምጽ መቅረጫ ቴፕ ሪከርደር፣ አንድ ፕሮፌሽናል የምስልና የድምፅ ማቀነባበሪያ እና አንድ ኮምፒውተር ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣ በኪራይ ለሚጠቀምበት እቃ የኪራዩን ጊዜ የሚያሳይ የኪራይ ውል፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ዋና እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ ወይም በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ቤት ለንግድ ሥራው ተስማሚ፣ እሳት ከሚያስነሱ ነገሮች የራቀ እና የሌሎችን አኗኗር የማያናጋ መሆኑ፣

#### *ለ. በውጪ ማስታወቂያዎች ማስታወቂያ የማሰራጨት ሥራ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች*

- ✓ በማርኬቲንግ፣ በጋዜጠኝነት ወይም በሌላ መሰል ትምሕርት ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው አንድ ባለሙያ መኖሩን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ዋና እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ ወይም በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ቤት ለንግድ ሥራው ተስማሚ፣ እሳት ከሚያስነሱ ነገሮች የራቀ እና የሌሎችን አኗኗር የማያናጋ መሆኑ፣
- ✓ አንድ የዲጂታል ፕሪንቲንግ ማሽን፣ እና
- ✓ አንድ ፕሮፌሽናል ቪዲዮ ካሜራ፣ አንድ ፕሮፌሽናል ፎቶ ካሜራ እና አንድ ኮምፒውተር ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣ በኪራይ ለሚጠቀምበት እቃ የኪራዩን ጊዜ የሚያሳይ የኪራይ ውል።

በተጨማሪም አመልካቹ የንግድ ሥራውን ሲጀምር  እንደሚያሟላቸው በመግለፅ የግዴታ ወረቀት የሚፈረምባቸው መስፈርቶች፡-

- ✓ የተሟላ የሥራ ሪከርድ እና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ እና ለምርመራ አስፈላጊ   በሆኑበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ ማድረግ፣
- ✓ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ ያለው፣ እና
- ✓ በማስታወቂያ ያሰራጫቸውን ወይም ያስተላለፏቸውን ማስታወቂያዎች ምስል፣ ድምጽ ወይም መልእክት ቢያንስ ለ30 ቀናት ቀርፆ ወይም በማናቸውም መንገድ ይዞ ማስቀመጥ፡፡

### *5. በሬዲዮ እና ቴሌቭዥን ሥራ ለመሰማራት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች*

- ✓ የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ፣
- ✓ የብሮድካስት መሳሪያዎችን በተመለከተ በኮምፒውተር ሳይንስ፣ በኤሌክትሪካል፣ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ የተመረቀ ቢያንስ አንድ ባለሙያ እንዲሁም የጋዜጠኝነት ሥራን በተመለከተ በማናቸውም ሙያዎች ቢያንስ በዲፕሎማ የተመረቁ በቂ ባለሙያዎች መኖራቸውንና የሰራተኞች ብዛት፣ የትምህርት ደረጃ እና የስራ ልምድ ማስረጃ፣
- ✓ የስቱዲዮ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ብዛት፣ አይነት እና የቴክኒክ ብቃት መኖር እና ዝርዝር ማስረጃ፣
- ✓ የማሰራጫ መሳሪያው ጉልበትና የአንቴናው ርዝመት አገልግሎቱን ለመስጠት በታቀደው አካባቢ ፕሮግራሞችን የማሰራጨት ብቃት፣
- ✓ የፕሮግራም ይዘት፣ የተካተቱ ማኅበራዊ፣ አገራዊና አካባቢያዊ ፕሮግራሞች ዝርዝር እና ለአገልግሎቱ የተመደበው የስርጭት ጊዜ፣
- ✓ ሥራው በሰው ጤና እና ደህንነት ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርስ ስለመሆኑ አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣

- ✓ ራው በሰው ጤናና ደህንነት ወይም በአካባቢ ላይ ጉደት የማያደርስ ስለ መሆኑ አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ማስረጃ
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ዋና እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ ወይም በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ቤት ለንግድ ሥራው ተስማሚ፣ እሳት ከሚያስነሱ ነገሮች የራቀ እና የሌሎችን አኗኗር የማያናጋ መሆኑ፣
- ✓ የካፒታል ምንጭ እና አቅም ማረጋገጫ መረጃው የጣቢያውን ብቃት እና ቀጣይነት የሚያረጋግጥ መሆኑ፣

***የአየር ሰአት ተከራይቶ ወይም በውል አግኝቶ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም የሚያሰራጭ አመልካች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-***

- ✓ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ መሆኑ ወይም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባላቸው ሰዎች የተቋቋመና በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ማኀበር መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
- ✓ ዋና አዘጋጁ በማናቸውም የትምሕርት መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ዋና እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ፣ በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣

**በተጨማሪም አመልካቹ የንግድ ሥራውን ሲጀምር እንደሚያሟላቸው በመግለፅ የግዴታ ወረቀት የሚፈረምባቸው መስፈርቶች፡-**

- ✓ የተሟላ የሥራ ሪከርድ እና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ እና ለምርመራ አስፈላጊ በሆኑበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ ማድረግ፣
- ✓ የሚጠቀምበት የሬዲዮና ቴሌቪዥን መሳሪያ የጥራትና የቴክኒክ ደረጃውን ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፣ እና
- ✓ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ ያለው መሆኑ።

### *6. የዜና ዘገባ ሥራ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች*

- ✓ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባላቸው ሰዎች የተቋቋመና በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ማኅበር መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ፣
- ✓ የብሮድካስት አገልግሎት ከሆነ ቢያንስ የኮሌጅ ዲፕሎማ ያለው አንድ ዋና አዘጋጅ፣ አንድ ምስል ቀራጭ፣ አንድ ድምፅ ቀራጭ፣ ሁለት ምስልና ድምፅ አቀነባባሪዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ባለሙያዎች መኖራቸውን የሚስረዳ ማስረጃ፣
- ✓ ቢያንስ አንድ ስቱዲዩ፣ አንድ የምስል እና የድምፅ ማቀነባበሪያ መሳሪያ፣ ፕሮፌሽናል ቪዲዮ ካሜራ እና ቢያንስ 5 የድምፅ መቅረጫዎች መኖር፣
- ✓ ለደንበኞቹ ዜና ለማሰራጨት የሚያስችለው የመረጃ መረብ ያለው መሆኑ።
- ✓ የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ዋና እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ የራስ ይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ፣ በኪራይ የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል፣

በተጨማሪም አመልካቹ የንግድ ሥራውን ሲጀምር የተሟላ የሥራ ሪከርድ እና ሠነዶችን አደራጅቶ እንደሚይዝ እና ለምርመራ አስፈላጊ በሆኑበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ እንደሚያደርግ የግዴታ ወረቀት ይፈርማል።

***በመገናኛ ብዙሃን እና ተያያዥ የንግድ ሥራ መደቦች ለመሰማራት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የሚያመለክት አመልካች መገንዘብ ያለበት ጉዳዮች፡-***

- ✓ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ እና የግዴታ ማስፈረሚያ ወረቀቶች በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፣
- ✓ የሙያ ብቃት መስፈርቶችን ማሟላት፣ መረጃዎችን በአግባቡ መሙላት እና ትክክለኛ ማስረጃዎችን እና አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ከማመልከቻ ቅፁ ጋር በማያያዝ ማቅረብ፣
- ✓ የንግድ ሥራ ሲጀምር እንደሚያሟላው በመግለፅ የግዴታ ምስክር ወረቀት የፈረመበትን ግዴታ ማክበር፣
- ✓ በሕግ የሚወሰነውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ክፍያ እና የምስክር ወረቀት ማደሻ ክፍያ መክፈል፣
- ✓ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሕግ መሰረት ካልተሰረዘ በስተቀር በየአመቱ የመንግስት በጀት አመት በተጠናቀቀ በ4 ወራት ውስጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲሰጥ ሊሟሉ የሚገቡ የሙያ ብቃት መስፈርቶችን በሟሟላት ማሳደስ፣ እና
- ✓ በማመልከቻ ቅፁና በማመልከቻው ላይ በገለፀው ወይም ባቀረበው መረጃ ላይ ማናቸውም አይነት ለውጥ ሲኖር ለውጡ በተፈጠረ በ15 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡